# የምርጫ ታሪክና የኢትዮጵያ ተሞክሮ

ተክለማርያም ተስፋማርያም

01-12-15

ሃሳብን በነፃነት መግለፅ እና በየጊዜው የሚከናወን ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የዴሞክራሲ መገለጫ ተብለው ከሚጠቀሱት ቀዳሚ መመዘኛዎች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ምርጫ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ህዝብን በመወከል ውሳኔ የሚያሳልፉ ወኪሎችን የመምረጥ ሂደትን የሚመለክት ሲሆን የተሻሻለው የምርጫ ህግ አዋጅ 532/1999 በአንቀጽ 1/4 ላይ እንደደነገገው “ምርጫ” ማለት በፌዴራልና በክልል ሕገ-መንግስታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣የአካባቢ፣የማሟያ ወይም  የድጋሚ ምርጫን የሚያመለክት ነው፡፡

በየትኛውም ጊዜና ቦታ ምርጫና የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም በጥብቅ የተቆራኙ ጉዳዮች ሲሆኑ የሚካሄዱ ምርጫዎች ግልጽ፣ነፃ፣ፍትሃዊና ሰላማዊ እንዲሆኑና መራጩ ህዝብ ስለ ተመራጮች ማንነትና ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲና ፕሮግራም በስፋት እንዲያወቅ፣ ይበጀኛል የሚለውን ለመምረጥ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ላይ እንዲደርስና  ምርጫው ፍሬያማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የሚረዳ መረጃና ዕውቀት ስለሚሰጡ መገናኛ ብዙሃን ያላቸው ሚና የጎላ ነው፡፡

በኢትዮጵያ አሁን ያለው የምርጫና የዴሞክራሲ ስርዓት ከሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ የታየ ክስተት ቢሆንም የምርጫ ታሪክ ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በተለይም ከአፄ ኃይለስላሴ ንግስና ጀምሮ  የታየ አሰራር ነው፡፡ በ2002 ዓ.ም. የወጣ  ምርጫ በኢትዮጵያ የተባለ መፅሄት እንደሚያስረዳው በ1923 ዓ.ም. በአፄ ኃይለስላሴ  የንግስና ዘመን በተካሄደው የመጀመሪያው የፓርላማ ምርጫ ወደ ፓርላማው እንዲገቡ የተደረጉት ተወካዮች በራሳቸው በንጉሱ የተመረጡ “መሳፍንቶች፣ መኳንንቶች፣ፊታውራሪዎችና በወቅቱ በነበረው አሰራር ባላባት የሚባሉት ነበሩ”፡፡

በወቅቱ የነበረው ሬዲዮም ንጉሱን  አምላክ የቀባቸው በማስመሰል የሚሰብክና የንጉሱን ታላቅነት በማወጅ ከእርሳቸው በቀር ማንም ችሎ አገር ሊያስተዳደር እንደማይችል ሌት ከቀን የሚለፍ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ነበር፡፡በዚያን ጊዜ ፓርላማው ወደ 250 የሚጠጉ

ተወካዮች የነበረው ሲሆን የስራ ዘመኑ በየአራት አመቱ በምርጫ የሚተካ ነበር፡፡እንደ መፅሄቱ ገለፃ ፓርላማው ከ1950 ዓ.ም.እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ህግ አርቃቂ፣ህግ አውጪና አስፈፃሚ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

እንደ መፅሄቱ ገለፃ ከንጉሱ ቀጥሎ ወታደራዊው ደርግ በ1966 ዓ.ም. ስልጣን ሲይዝ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የተጠቀመበት መንገድ ጉልበትና መሳሪያ ነበር፡፡ ወታደራዊው ደርግ የሚመራው መንግስት የለየለት አፋኝ በመሆኑ በአፄ ኃይለስላሴ ጊዜ ታይቶ የነበረውን የዲሞክራሲና የመቻቻል ጭላንጭል ጨርሶ ዘግቶታል፡፡በዚህም ምክንያት የዴሞክራሲ አካል ለሆኑት ሃሳብን በነፃ የመግለጽና የመሰብሰብ መብቶች ምንም ቦታ አልነበረውም፡፡

የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሃይል ከመደፍጠጡም በላይ እንደስጋት የሚያያቸውን አያሌ የመብት ተሟጋቾች፣ ወጣቶችና የመንግስት ሰራተኞች በግፍ እንደገደለ አያሌ የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ፡፡ ይሁንና በወቅቱ የነበሩት መገናኛ ብዙሃን የነበረውን ግድያ፣አፈናና ጭቆና ከማውገዝና ከመቃዎም ይልቅ የደርጉን ተራማጅነትና ለጭቁኖች የቆመ መሆኑን የሚለፈልፉ የስርዓቱ መሳሪያዎች ነበሩ፡፡

ደርግ በህዝባዊ ትግል ከተወገደ  ከ1983 ዓ.ም. በኋላ የጀመረው ህዝባዊና ዴሞክራሲዊ መንግስት ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ለመወከልና ከፓርላማ ወኪልነት እስከ ቀበሌ አመራርነት ለማሳተፍ የሚያስችል አዲስ የምርጫ አሰራር ይዞ ብቅ አለ፡፡በዚህም መሰረት ዕድሜው 18 ዓመት የሞላ እና በአካባቢው ሁለት ዓመት የኖረ ኢትዮጵዊ ሁሉ በምርጫ እንዲሳተፍ የሚያስችል አዋጅ 11/1984 በመውጣቱ ሁሉም ኢትዮጵዊ በነቂስ መመዝገብና በምርጫ መሳተፍ ቻለ፡፡

ይህንን ተከትሎ ቀደም ባሉት ጊዜያት  የገዢዎች የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ የነበሩት የመገናኛ ብዙሃን ሁሉንም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች እኩል ማገልገልና ለመራጩ ህዝብ መረጃ በነጻነት መስጠት ጀመሩ፡፡ይህም ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ያላቸውን ፕሮግራም ለህዝብ በማቅረብ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እና የምረጡኝ ቅስቀሳ እንዲያካሂዱ ረድቷቸዋል፡፡

በኢ.ፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የህዝብ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ እንዲመሩ ይደረጋል ተብሎ ስለተደነገገ እና የመገናኛ ብዙሃን የህዝብ ሀብት በመሆናቸው መራጩ ህዝብ ከቀረቡለት አማራጮች ውስጥ ይበጀኛል የሚለውን በመቀበል ለምርጫ ውሳኔ ላይ የሚያደርሰውን መረጃ በእነሱ አማካይነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ 532/1999 ቁጥር 59/1 ተወዳዳሪ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች መገናኛ ብዙሃንን ያለአድልዎ የመጠቀም መብት አላቸው በማለት ሲገልፅ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/99 በአንቀጽ 43 በበኩሉ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለህዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዴሞክራሲዊ ተልዕኮዎች ለማሳካትም መገናኛ ብዙኃን ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለህዝቡ በመስጠት የውይይትና የክርክር መድረክ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ አስተያየቶችን ለህዝቡ በማቅረብ በነፃ እንዲንሸራሸሩ በማድረግ በውይይቶችና ክርክሮች ሂደት ተፈላጊው የጋራ እምነትና አመለካከት እንዲጠናከር ይረዳሉ፡፡

## የመገናኛ ብዙሃን ሚና ከምርጫ አንፃር

ባለፉት ምርጫዎች የመገናኛ ብዙኀን ለተለያዩ ፓርቲዎች ነጻ የአየር ጊዜና የጋዜጣ አምድ መድበው የምረጡኝ ቅስቀሳዎችን በማቅረብ፣ የፓርቲዎችን የክርክር መድረኮች በማመቻቸት፣ ምርጫ-ነክ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን በማስተላለፍ ምርጫው ነጻ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን ገንቢ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ለአብነትም በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ሃገራዊ ምርጫ አራት የብሮድካስት ጣቢያዎች ማለትም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ የኢትዮጵያ ሬድዮ፣ ሬድዮ ፋና ብሄራዊ አገልግሎት እና ሬድዮ ወያነ ትግራይ ላይ ነጻ የአየር ጊዜ መድበው የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩ ተወዳዳሪዎችን የምርጫ ቅስቀሳ ከጥር 12 እስከ ግንቦት 14/1997 ዓ.ም. ድረስ ሲዘግቡ ቆይተዋል፡፡

ብሮድካስተሮች ከምርጫው ጋር ተያያዥ የሆኑ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን ከአድልዎ በጸዳና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማቅረባቸውና የምርጫ ሕጎችን አክብረው በመስራታቸው ፓርቲዎች የተደመደበላቸውን ነፃ የአየር ሰዓት በፍትሃዊነት ለመጠቀም ችለዋል፡፡

የብሮድካስት መገናኛ ብዙኀን በምርጫው ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች ያካሄዱትን 14 የክርክር መድረኮችን በማመቻቸትና በፍትሃዊነት በማስተናገድ መራጩ ሕዝብ በተወዳዳሪ ፓርቲዎች ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው የበኩላቸውን ድርሻ አበርክተዋል፡፡

እነዚህ መገናኛ ብዙሃን በ1997 በተካሄደው ምርጫ ያበረከቱት አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጥታ ስርጭት በተላለፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ክርክር መድረኮች ላይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከማስተዋወቅ ይልቅ ሌሎች ፓርቲዎችን የማጥላላት፣የጥላቻ ንግግር (hate speech) ማድረግና የግለሰቦችን ስብዕና የማንኳሰስ አካሄድ ተከስቶ ነበር::ከዚህም በላይ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸው የምረጡኝ ቅስቀሳዎች የምርጫ ሕጉንና ሌሎች የሃገሪቱን ሕጎች የጣሰ ይዘት ቢኖራቸውም የተስተናገዱበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

ቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ በ2002 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን በዚህ ምርጫ የብሮድካስት መገናኛ ብዙኀን ነፃ የአየር ጊዜ በመመደብ፣ የክርክር መድረኮችን በማመቻቸትና ምርጫ ነክ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን በማቅረብ ለምርጫው ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ለምርጫ ቅስቀሳ ነፃ የአየር ጊዜ የተመደበው ሃገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ በሆኑ የመንግስትና የግል ብሮድካስት ጣቢያዎች ላይ ሲሆን የግሉ ብሮድካስትም ጭምር ለመገናኛ ብዙሃን በተደለደለ ነጻ የአየር ጊዜ መሰረት ፓርቲዎችን በማስተናገድ ፖሊሲና አማራጮቻቸውን ለመራጩ ሕዝብ ማድረስ እንዲችሉ አድርገዋል፡፡

በተጨማሪም የቅስቀሳ ፕሮግራሞቻቸውን ብሮድካስተሮች በሚጠይቁት ፎርማት ለማቅረብ ላልቻሉ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በራሳቸው ስቱዲዮ እንዲዘጋጅላቸው ተደርጓል፤ የብሮድካስት የምርጫ ዴስክ ተቋቁሞ የምርጫውን ሂደት በተከታታይ ሲዘግብ ቆይቷል፡፡ ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በሚያስተላልፈው ተመሳሳይ ፕሮግራም ላይ 11 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ፓርቲዎቹ 27 ሰዓት የፈጀ ክርክር በ9 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አካሂደው ፖሊሲና ስትራቴጂዎቻቸውን ለመራጩ ህዝብ ለማስረዳት ችለዋል፡፡

በዚህ ሂደት ብሮድካስተሮች ለፓርቲዎች በተመደበው ነፃ የአየር ጊዜ መሰረት የቅስቀሳ ፕሮግራሞቻቸውን አሰራጭተዋል፡፡ በሃገራዊና ክልላዊ የብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያዎች የተሰራጩ ቅስቀሳዎች ይዘትም ፓርቲዎች የተሻለ አማራጭ እንዳላቸው የሚቀሰቅሱና ገዥውን ፓርቲ በመተቸት ላይ ያነጣጠሩ ሆኖ በአንጻራዊነት የጎላ ችግር የተስተዋለባቸው አልነበሩም፡፡

ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰው ብሮድካስተሮች የራሳቸውን የምርጫ ዴስክ በማቋቋማቸውና የቅስቀሳ ይዘቶች ከምርጫ ሕጉና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ሕጎችና መመሪያዎች ጋር የማይጋጩ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለስርጭት በማብቃታቸው ነው፡፡ የምርጫ ሕጉንና ሌሎች ሕጎችን ያላገናዘቡ ሕገ-ወጥ ቅስቀሳዎች ሲቀርቡ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት አስተካክለው እንዲያቀርቡ በማድረግ ለምርጫ ቅስቀሳው ሂደት መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች በኩል የቀረበ ቅሬታም እንደሌለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከምረጡኝ ቅስቀሳው በተጨማሪ የብሮድካስት መገናኛ ብዙኀን የምርጫ ነክ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን በሰፊው በማቅረብ በምርጫው ሂት ለሕዝቡ ተገቢውን መረጃና ትምህርት በመስጠት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የክርክር መድረኮች በማዘጋጀት በክርክሩ ሂደትም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ በዜና፣ ዜና ትንታኔ፣ በዜና መጽሄትና ሰፊ ሽፋን ተሰጥቷል፡፡

የምርጫ ነክ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን በተመለከተ ከሞላ ጎደል ሁሉም ብሮድካስተሮች ሰፊ ሽፋን ሰጥተው ዘግበዋል፡፡ ከሚዛናዊነትና ከገለልተኝነት አንጻር በተወሰኑ ጣቢያዎች ከታዩ ችግሮች በስተቀር በአብዛኛው በጥሩ አፈፃፀም ነበረው፡፡ በተለይም የኦሮሚያና የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅቶች በምርጫው ዕለት በተለያዩ አካባቢዎች ሪፖርተሮችን በመላክ የምርጫውን ሂደት ቀኑን ሙሉ በቀጥታ ሲዘግቡ ውለዋል፡፡

የህትመት ሚዲያዎችም ቢሆኑ እንደ ብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ሁሉ በተለያየ ጊዜያት የተካሄዱትን ሀገራዊ ምርጫዎች በስፋት ዘግበዋል፡፡ ለምሳሌ በ2002 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ በተለይም የሕዝብ ሕትመት ሚዲያዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ ነጻ የጋዜጣ አምድ መድበው ቅስቀሳዎቻቸውን በማቅረብና የምርጫውን ሂደት ለመራጩ ሕዝብ በማድረስ የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡

ይሁንና በየጊዜው የሚወጡ ሕትመቶችን በተመለከተ የተደረጉ የሞኒተሪንግ ውጤቶች እንደሚያሳዩት አብዛኛዎቹ የህትመት ውጤቶች የገለልተኛነትና የፍትሃዊነት ችግር ነበረባቸው፡፡ይሁንና ይህ ችግር በ1997 ዓ.ም. ከነበረው ሰፊ ችግር አንፃር ሲታይ አበረታች ለውጥ አሳይቷል፡፡

## ነፃ የአየር ሰዓትና የጋዜጣ አምድ አመዳደብ መርህ

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች አንቀጽ 21 መሰረት ማንኛውም ሰው በሃገሩ የመንግስት ስልጣን ጉዳይ ላይ በቀጥታም ሆነ በተወካዮቹ አማካኝነት የመሳተፍ መብት እንዳለውና ይህም የሚገለፀው በየጊዜው በሚከናወን ምርጫ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንን ዓለማቀፋዊ ድንጋጌና ሌሎች አገራዊ ህጎች መሰረት በማድረግ በምርጫ ወቅት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ነፃ የአየር ሰዓት ወይም የጋዜጣ አምድ የመደልደል ጉዳይ በሌሎች አገሮችም የተለመደ አሰራር ነው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲና ፕሮግራምቻቸውን ለመራጩ ሕዝብ ለማስተዋወቅ ይረዳቸው ዘንድ በህዝብ የመገናኛ ብዙሃን ለመጠቀም የሚረዳ ነፃ የአየር ሰዓትና የጋዜጣ አምድ ምደባ በሚካሄድበት ወቅት እንደየአገሮች ተጨባጭ ሁኔታ ሁለት ዓይነት የድልድል መርሆችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡መርሆቹም የአየር ሰዓቱን እኩል (equally) የመደልደል ወይም የአየር ሰዓቱን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መደልደልን (equity) መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የእኩል ድልድል መርህ ማለት ለውድድር የተመዘገበ ማንኛዉም ፓርቲም ሆነ ዕጩ ተወዳዳሪ እኩል ነጻ የአየር ሰዓትና የጋዜጣ አምድ የሚያገኝበት አማራጭ ነው፡፡ ይህ አማራጭ የመድብለ-ፓርቲ ስርዓትና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚካሄድባቸው እንዲሁም ተወዳዳሪዎች ያላቸዉን የሕዝብ ድጋፍ ለማወቅ በማይቻልበት ጊዜ የሚሰራበት ነው፡፡ይህንን አማራጭ ከሚከተሉ አገሮች ውስጥ ፈረንሳይ፣ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ጣሊያን፣ጃፓንና ኔዘርላንድስ ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ የምደባ መርህ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ የሆነ ነፃ የአየር ሰዓት ለመመደብ

ከግንዛቤ ውስጥ የሚገቡት ባለፈው ምርጫ ፓርቲው የነበረው ጥንካሬ እና ያቀረባቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት የሚሉት ናቸው፡፡

የፍትሃዊነት ድልድል መርህ ሁሉም መገናኛ ብዙኀን ተቋማት የተለያዩ አስተሳሰቦች ለማንሸራሸር እንዲችሉ ለሁሉም ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ የሆነ ዕድል መሰጠት አለባቸዉ የሚል አማራጭ ሲሆን መገለጫዎቹም ለምርጫ ዘመቻ ውድድር የተመደበውን አጠቃላይ ነፃ የአየር ሰዓት ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ባላቸዉ የሕዝብ ድጋፍ እንዲከፋፈሉ የሚደረግበት ነው፡፡ይህ አሰራር በተለይም የዴሞክራሲያዊ የምርጫ ውድድር የመጀመሪያቸዉ ባልሆኑ ሃገሮች የሚሰራበት አማራጭ ነው፡፡ፍትሐዊ የድልድል አማራጭ ተግባራዊ ከሚያደርጉት አገሮች ውስጥ እስራኤል፣ ቱርክ ፣ዩናይትድ ኪንግደም፣ ስፔንና ቱርክ ይጠቀሳሉ፡፡
ሁሉም መርሆዎች በተለያዩ አገራት ተፈጻሚ ቢሆኑም የአንዱ መርህ ተከታዮች የሌላውን መርህ አግባብነት በሚመለከት ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ በመርሆዎቹ ላይም ክርክር ያቀርባሉ፡፡ የአየር ሰዓቱም  መደልደል ያለበት ለሁሉም ተወዳደሪዎች እኩል መሆን አለበት ወይስ የለበትም፤ ፍትሐዊ ቢሆን አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚል አቋም ባላቸው ወገኖች መካከል ነው፡፡ ሁለቱ ወገኞች የሚያቀርቡት መከራከሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ነፃ የአየር ሰዓቱ እኩል መደልደል አለበት የሚሉ ወገኖች የሚያቀርቡት ማሳመኛ ኃሳብ ዕጩ ተወዳዳሪው የምርጫ ውድድሩን የሚያቀርበው ለመራጩ ሕዝብ እንጂ ለሚዲያው ወይም ሚዲያውን ለሚቆጣጠረው አካል አይደለም፡፡ ድልድሉም ቀላልና ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል ነው የሚል ነው፡፡ በተቃራኒው በእኩል ደረጃ ሊከፋፈል አይገባም የሚሉ ወገኖች የሚያቀርቡት ኃሳብ በአገሪቷ ወሳኝ የፖሊሲ አቅጣጫ ያላቸው ፓርቲዎች ሃሳብ እንዳይደመጥ ከማድረግና ጊዜውን ከማባከብ ውጭ የሚኖረው ፋይዳ የለም፡፡ የአየር ሰዓቱ እኩል ተደልድሎ ከተሰጠ መራጩ ሕዝብ የሚቀርብለትን ሁሉንም ኃሳብ እንዲወስድ ማስገደድና ድርጊቱም አሰልቺ ስለሚሆን ወደማይመርጥበት ደረጃ ያደርሰዋል የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡

በሌላ በኩል ፍትሐዊ ድልድልን የሚደግፉ ወገኖች የሚሰጡት ምክንያት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ባላቸው የሕዝብ ድጋፍ መነሻነት ለመራጩ ሕዝብ ፖሊሲና ፕሮግራማቸውን በበቂ መጠን ለማስረዳት ይረዳቸዋል፡፡ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ የሚያበቃቸውን ድምፅ ለማግኘት ተስፋ ያላቸው ጠንካራ ፓርቲዎችን ኃሳብ ለማድመጥ

እንዲሁም አነስተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያላቸውን ፓርቲዎች ይሁንታን እንዲቸራቸው ለማድረግ ያስችላል የሚል ነው፡፡

ነገር ግን ይህ አስተሳሰብም ተቀዋሚ ሃሳብ አላጣም፡፡ በፍትሀዊነት ድልድል የሚነሳው ተቃራኒ ሃሳብ የፍትሃዊነት ድልድል መርህ አነስተኛ እጩ ተወዳዳሪና አዳዲስ ፓርቲዎች በበቂ ሁኔታ እንዳይደመጡ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የፍትሃዊነት መርህ በራሱ ፍትሃዊ አይደለም በማለት የእኩልነት መርህ አራማጆች ይከረከራሉ፡፡

ከላይ የቀረቡት ሁለቱ ተቃራኒ ሃሳቦች በየራሳቸው ተቀባይነት ሊኖራቸው ስለሚችል አንዱ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም መርሆዎች እንደየአገራቱ ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጎት ተግባራዊ እየተደረጉ በመሆኑ ነው፡፡ ተግባራዊ ሲደረጉ ከግምት መግባት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች ግን ይኖራሉ፡፡
እነርሱም የእኩልነት መርህን በመከተል የአየር ሰዓትም ሆነ የጋዜጣ አምድ ለመደልደል የሚቻለውና ውጤታማም የሚሆነው በአገሪቱ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በሚሳተፉበት ምርጫ ወቅት ይሆናል፡፡ ብዛት ያላቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ባሉበት አገር ነጻ የአየር ሰዓቱን እኩል ቦታ ለመደልደል መሞከር አንድን ኬክ ማከፋፈል በማይቻልበት ደረጃ መቆራረስ ይሆናል፡፡

ለአገሪቱ ልማትና ዲሞክራሲዊ እድገት ወሳኝ የሆነ ፖሊሲ ያላቸው ተወዳደሪዎችም በመራጩ ህዝብ የመደመጥ እድልን ስለሚሳያጣ መርሁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡

የፍትሀዊነት መርህ ሊሰራ የሚችለውም ከዚህ በፊት ተከናውኖ በነበረው ምርጫ በምክር ቤት ባላቸው መቀመጫ፤ ለአሁኑ ምርጫ ውድድር ባስመዘገቧቸው እጩዎች ብዛትን መሰረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ይዞ መንግስት የመሰረተ ፓርቲ ስላከናወናቸው ተግባራት ለመራጩ የሚያስረዳበት በቂ ጊዜ ሊሰጠውና በአሁኑ ምርጫም አብላጫ መቀመጫ መያዝ የሚያስችላቸው እጩ ተወዳዳሪ ያቀረቡ ፓርቲዎችን ሃሳብ በመራጩ ህዝብ እንዲደመጡ ለማስቻል ነው በማለት የፍትሃዊነት መርህ ደጋፊዎች ይከራከራሉ፡፡

## በመጪው ምርጫ መገናኛ ብዙሃን ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ምንም እንኳን ፍትሃዊ የምርጫ አሰራር ሂደት በሀገራችን ውስጥ ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ እያበበ የሚገኝ ዴሞክራሲያዊ ትሩፋት ቢሆንም በመጪው ግንቦት 2007 ዓ.ም. የሚካሄደውን አገራዊ ምርጫ በስኬት ለማጠናቀቅ በፊት የተገኙት ተሞክሮዎች የራሳቸው ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በፊት ከተገኙት ተሞክሮዎች ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን የሰዓትና የጋዜጣ አምድ ድልድልና አጠቃቀም አንዱ ነው፡፡ በምርጫ ወቅት ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመደብ ነፃ የአየር ሰዓት በዋናነት በሁለት መርሆች ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ እነዚህም የፍትሃዊነትና የእኩልነት መርህ ናቸው፡፡

የፍትሃዊነት መርህ ማለት ለምርጫ ቅስቀሳ ከተመደበው ነጻ የአየር ጊዜ፣ የጋዜጣ አምድ ውስጥ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባላቸው የም/ቤት መቀመጫ እና ባስመዘገቡት እጩ ብዛት ተመስርቶ የሚከፋፈል ነው፡፡ የእኩልነት መርህ ደግሞ ለምርጫ የቀረቡ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ የአየር ሰዓት/የጋዜጣ አምድ እኩል የሚከፋፈሉበት መርህ ነው፡፡

የእኩልነት መርህ በብዙ ሃገራት ተግባራዊ የሚደረገው ለመጀመሪያ ጊዜ ምርጫ ለሚያካሂዱ ሀገራት፣ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚወዳደሩበት ሀገራትና ፕሬዝዳንታዊ ምርጫን በሚያካሂዱ ሃገራት ነው፡፡ በአንጻሩ የፍትሃዊነት መርህ ተግባራዊ የሚያደርጉት ፓርላሜንታዊ ስርዓትን የሚከተሉ ሃገራት ናቸው፡፡

ለአብነትም በ1997 ዓ.ም. በተካሄደው አገራዊ ምርጫ ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሬድዮ ከተመደበው 135 ሠዓት ከ57 ደቂቃ ውስጥ 82 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ቀሪው 53 ሰዓት ከ46 ደቂቃ ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ኢህአዴግ 60 ሰዓት ከ 42 ደቂቃ ተመድቦለት 36 ሰዓት ከ3 ደቂቃ የተጠቀመ ሲሆን ተወዳዳሪ ፓርቲዎች 75 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ተመድቦላቸው 46 ሰዓት ከ7 ደቂቃ ተጠቅመዋል፡፡ ቀሪው 29 ሰዓት ከ7 ደቂቃ ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን መረጃዎች እንደሚያሳዩት በ2002 ዓ.ም. ምርጫ 490 የሬዲዮ እና 87.18 የቴሌቪዥን ሰዓት እንዲሁም 776 የጋዜጣ አምድ ተመድቦ የነበረ ሲሆን ይህም በገንዘብ ሲሰላ ከ38 ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ጥቅም ላይ ያዋሉት በሬዲዮ 267.13 እንዲሁም በቴሌቪዥን 57.14 ሰዓታት እና በጋዜጣ 326 አምዶችን ብቻ ነው፡፡

ሃሳቡን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የአየር ሰአትና የጋዜጣ አምድ ድልድልና አጠቃቀም ማሳያ የሚሆን ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

<u>ነፃ የአየር ሰዓት አጠቃቀም ማሳያ(ቴሌቪዥንና ሬዲዮ)</u>

| ተ.ቁ. | የምርጫው ዓመት | የፖለቲካ ፓርቲ ሥም | የተመደበለት የአየር ሰዓት በደቂቃ | የተጠቀመበት | % አጠቃቀም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1997 | <u>ነጻ የዓየር ሰዓት</u> | | | |
| | | ኢ.ህአዲግ | 2451 | 1985፡44 | 81% |
| | | አጋር ድርጅቶች | ------------ | ------------ | --------- |
| | | ተቃዋሚዎች | 4383፡51 | 2729 | 62% |
| 2 | 2000 | ኢ.ህአዴግ | 4380 | 2818፡34 | 64.4% |
| | | አጋር ድርጅቶች | 1273፡50 | 273፡10 | 19 % |
| | | ተቃዋሚ ፓርቲዎች | 5066፡50 | 2026፡28 | 39% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | 2005 | ኢ.ህአዴግ | 13፡06፡00 | 10፡19፡04 | 75% |
| | | አጋር ድርጅቶች | 06፡16፡00 | 02፡20፡00 | 32.4% |
| | | ተቃዋሚ ፓርቲዎች | 12፡01፡00 | 06፡04፡00 | 50.3% |

የተመደበ ነጻ ነፃ የጋዜጣ አምድና ጥቅም ላይ የዋለ

| የፓርቲው ስም | የተመደበለት አምድ | የተጠቀመበት አምድ | የተጠቀመበት በመቶኛ | ያልተጠቀመበት አምድ | ያልተጠቀመበት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢ.ህአዴግ | 42 | 26 | 62% | 16 | 38% |
| ተቃዋሚ ፓርቲዎች | 40 | 18 | 45% | 22 | 55% |
| አጋር ፓርቲዎች | 14 | 2 | 14.3% | 12 | 85.7% |
| ድምር | 96 | 46 | 48% | 50 | 52% |

ከዚህ አኳያ በመጪው የምርጫ ወቅት ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመደበው ነጻ የአየር ሰዓትና የጋዜጣ አምድ ሀገራዊ ሃብት በመሆኑ ካለፈው ልምድ በመማር ሁሉም የፖለቲካ ፓርተዊዎች በተገቢው ሁኔታ በስራ ላይ እንዲያውሉት ያስፈልጋል፡፡

መገናኛ ብዙኃን በዴሞክራሲዊ የምርጫ ሂደት ውስጥ የህዝብ ተሳትፎን በማበረታታት፤ህዝቡ ለድምጽ አሰጣጥ ውሳኔው የሚያግዙትን የተሟላ መረጃዎች በማቅረብ ተሳትፎውን በንቃት እንዲያከናውን በተጨማሪም የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርቶችን በማስተላለፍ አብይ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ይህን ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻልና የምርጫ ዘገባዎች አቀራረብ ገለልተኛና ሚዛናዊ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚዛናዊ የሆነ የአየር ጊዜ እንዲያገኙ ለማድረግ የምርጫ-ነክ የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎቶችን አግባብነት መከታተል፤ መቆጣጠርና ተገቢው የማስተካከያ ርምጃ የሚወሰድበት አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

ምርጫን በተመለከተ ለመራጩ ህዝብ ትምህርትና ቅስቀሳ ተደራሽ በማድረግ በኩል የመገናኛ ብዙሃን ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ቢሆንም ያለፉትን ተሞክሮዎች መሰረት በማድረግ በ2007 ዓ.ም. የሚካሄደውን አገር አቀፍ ምርጫ ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ከበፊቱ የበለጠ ቅድመ-ዝግጅትና ምርጫውን ታሳቢ ያደረገ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ ስለምርጫ በቂ ግንዛቤ በመያዝ ተሳታፊ እንዲሆን ለማስቻል እነዚህ ተቋማት የመራጮችና የዕጩዎች ምዝገባ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለመራጩ ህዝብ ምርጫ-ነክ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 29 ኃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ቢረጋገጥም ይህ ነፃነት ፍፁማዊ ባለመሆኑ በህገ መንግሥታችን አንቀጽ 29(6) መሠረት ገደብ ሊጣልበት የሚችል ነው፡፡ሃሳብን በነፃ በሚገለጽበት ጊዜ በተለይ በብሮድካስት ሚዲያው ሲሰራጭ በብሮድካስት አዋጅ አንቀጽ 30(4) የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበር አለባቸው ወይም ሊጣሱ አይገባም፡፡ የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት በምርጫ ወቅትም እንደተጠበቀ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጥላቻ አዘል ቅስቀሳ (hate speech) ቅራኔ ከመፍጠር ውጪ ለዴሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ ፋይዳ የሌለው በመሆኑ እንደዚህ አይነት ቅስቀሳዎችን ከማድረግ መቆጠብና ጥላቻን የሚነዛ ወይም ህገ-ወጥ ዘገባ ለመገናኛ ብዙሃኑ ሲቀርብላቸው አላሰራጭም የማለት መብታቸውን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ይሁን እንጂ አላሰራጭም ያለበትን ምክንያትም በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘገባው እንዲሰራጭ ላቀረበው ተወዳዳሪ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ አስተሳሰብ ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቱ እመዝኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በሀገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የስርጭት ጊዜ የተሰጠው የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ተወዳዳሪ ለተሰራጨው ፕሮግራም ወይም መግለጫ ህጋዊ ሃላፊነት እንዳለበት የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ አንቀጽ 43(4) ይደነግጋል፡፡

ለአብነትም ያህል በ2000 ዓ.ም. ተከናውኖ በነበረው የአካባቢ እና የማሟያ ምርጫ ወቅት ጥላቻን የሚነዛ ዘገባ ወይም በአጠቃላይ ህገ ወጥ ዘገባ ለመገናኛ ብዙሃኑ ሲቀርብለት አላሰራጭም የማለት መብት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌን ከማስከበር አንጻር በህግ ገደብ የተጣለባቸውን ድንጋጌዎች በመጣስ ጥላቻ-አዘል ቅስቀሳ ለማስተላለፍ የሚፈልግ ፓርቲ ካለ ተስተካክሎ እስኪቀርብ ድረስ መገናኛ ብዙኀኑ የምርጫ ቅስቀሳ ፕሮግራሙን አላስተላልፍም የማለት ህጋዊ መብት አላቸው፡፡

ያለፉትን የምርጫ ልምዶች ከግምት ውስጥ በማስገባትና በምርጫ ወቅት ሊኖር የሚገባውን የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም መመሪያዎች መነሻ በማድረግ እንዲሁም የሌሎች አገራትን ተሞክሮዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በ2007 ዓ.ም. ለሚከናወነው አገራዊ ምርጫ የሚያገለግል መመሪያ ከወዲሁ በማዘጋጀት ተወዳዳሪ ፓርቲዎች እንዲወያዩበት ማድረግ ጠቀሜታው አጠያያቂ አይደለም፡፡

መጪው ምርጫ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ውድድር በመሆኑ መራጩ ህዝብ ትክክለኛ መረጃ እንዲኖረው ከማስቻል አንጻር ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከጥላቻ የፀዳ ቅስቀሳ ማቅረብ ሕገ-መንግስታዊ ግዴታቸው በመሆኑ ፕሮግራሞቻቸውን ለማሰራጨት ወደ መገናኛ ብዙኃን በሚቀርቡበት ወቅት ልዩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማስቻል የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና የፓርቲ ተወካዮች ምርጫን አስመልክቶ ስለመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር ጠቃሚ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫን የተመለከተ ጉዳይ በዋናነት የሚመለከተው ስለሆነ በስነምግባር ደንቦች ላይም ይሁን በሚዲያ አጠቃቀም ላይ ፓርቲዎችንና የመገናኛ ብዘሃን አካላትን ማሰልጠንና የህዝቡን ግንዛቤ በማዳበር

መጪውን ምርጫ ሰላማዊና ፍትሃዊ ሊያደርጉ የሚችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የምርጫ ቁሳቁሶችን በተገቢው ሁኔታ አስቀድሞ ለማዘጋጀትና የምርጫ ፕሮግራሞችን ለማሳወቅ ደረገው ጥረት አበረታች ቢሆንም ምርጫው ፍትሃዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይም ምርጫን በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዘቤ ሊያዳብሩ የሚችሉ ትምህርታዊ ስልጠናዎችን በስፋት  መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ ዋና ባለድርሻ አካል በመሆኑ የአየር ሰዓትና የጋዜጣ አምድ ድልድሉ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚረዳ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግና ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የሚያደርጉት ቅስቀሳ የህዝቡን ንቃተ-ህሊና በማሳደግ ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲደርግ ለመገናኛ ብዙሃን የሚያደርገውን ስልጠናና የአቅም ግንባታ ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በተለይም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች፣ህብረተሰቡና መንግስት መጪው ሀገራዊ ምርጫ በስኬት እንዲጠናቅ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ስለአላቸው ከምንጊዜውም በበለጠ በትብብር መስራትና ያላቸውን አቅም በመጠቀም ምርጫን በተመለከተ የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ አሰራር ወደፊት የሚያራምድ ተግባር ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡

ያለፈው ምርጫ ሰላማዊና ዴሞክራሲዊ ሆኖ የተጠናቀቀው በህዝቡ የነቃ ተሳትፎ በመሆኑ ይህንን መልካም ተሞክሮ ወደፊት ባሉት ምርጫዎች አጠናክሮ እንዲቀጥል ይጠበቃል፡፡

ከምንም በላይ የዴሞክራሲያዊ ምርጫና የሰላም ተጠቃሚ ህዝቡ በመሆኑ ለምርጫ ያለውን ግንዛቤ በማጎልበት በመጪው አገራዊ ምርጫ በንቃት መሳተፍና የምርጫውን ዴሞክራሲዊነትና ሰላማዊ አካሄድ ሊፈታተኑ የሚችሉ ነገሮችን ነቅቶ በመከታተልና ችግሮች ሲያጋጥሙ ነቅሶ በማውጣት ወደ ህግ ፊት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡